ሞዓ አንበሳ

Moa Anbessa

ዙፋናዊ አሰባሳቢ አካል

ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም.

የዓፄ አምኃ ሥላሴን ዜና ዕረፍት ምክንያት በማድረግ ስለ ግርማዊነታቸው የኀይወት ታሪክ የተሠጠ አጭር መግለጫ

ዓፄ አምኃ ሥላሴ ሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፰ ዓ. ም. ከገናናው አባታቸው ከዓፄ ኃይለ ሥላሴና ከእናታቸው ከግርማዊት ዕቴጌ መነን አዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። ለልዑላን ንጉሣውያን ቤተሰብ በሚደረገው ከፍተኛ እንክብካቤ በሥነ ምግባር በሞራል በሃይማኖት በትምህርትና በስፖርት ታንፀው አደገዋል። ገና በወጣትነታቸው በአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜያቸው አባታቸው ዓፄ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ሲቀዳጁ እርሳቸውም መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን በመባል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ሆነዋል።

በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ፋሺስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን መጀመሪያ ጠላትን ለመመከት ማይጨው ላይ በተደረገው ታላቅ ጦርነት ተካፋይ በመሆን ከዚያም ጣሊያኖች በዓለም መንግሥታት በተከለከለ የመርዝ ጋዝ ጪስ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ በመርጨታቸው ጦሩ ሲፈታ አቤቱታ ለማቅረብ ከአባታቸው ጋር ወደ እንግሊዝ አገር በመሰደድ አምስቱን የጠላት ወረራ ዘመን አሳልፈዋል። በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ፋሺስት ጣሊያን ከኢትዮጵያ ተባርሮ ኢትዮጵያ እንደገና ነፃነትዋን ስትቀዳጅ ከአባታቸው ጋር በድል አድራጊነት አገራቸው ተመልሰው በአልጋ ወራሺነታቸው የአባታቸው የቅርብ ረዳት በመሆን ለኢትዮጵያ የሥልጣኔ እርምጃ በተደረገው ተጋድሎ ሁሉ ተካፋይ በመሆን በተላያዩ የሥራ ረድፎች አገራቸውን በቅንነት አገልግለዋል። በተለይም በበጌምድርና ሰሜን በትግሬና በወሎ ጠ/ግዛቶች በአገረገዥነት ጭምር በአገለገሉበት ረጅም ዘመናት እነዚህ ጠ/ግዛቶች በትምህርት ቤቶች መስፋፋት በሆስፒታሎች መቋቋም በመንገዶች መዘርጋት ብዙ እርምጃዎች አይተዋል። አያሌ ለሕዝብ ጠቃሚ የሆኑ ሥራዎችንም አከናውነዋል። ብዙ ጊዜ ከአባታቸው ጋር በመሆን አንዳንድ ጊዜም አባታቸውን በመወከል ብቻቸውን ብዙ የውጭ አገሮችን በመዘዋወር በመጎብኘት ለአገር ሥልጣኔና እርምጃ ጠቃሚ የሆኑ ዕቅዶችንና ትምህርቶችን ቀስመዋል።

ዓፄ አምኃ ሥላሴ በመልካም አስተዳዳሪነታቸውና ሚዛናዊ በሆነ የዳኝነት ተሠጧቸው እንዲሁም በቸርነታቸው በሕዝብ ዘንድ እጅግ የተወደዱ ነበሩ። በዚህም ምክንያት በሃገራቸው ምድር ላይ ዘውድ ጭነው በሙሉ ሥልጣን አገሪቱን የሚያስተዳድሩበትን ሰዓትና ቀን የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ ተስፋና ጉጉት ሲጠባበቅ ነበረ። አሁን ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ይህን ተስፋና ምኞት በሥራ ላይ ሳይውል በታሪክ ብቻ ተመዝግቦ እንዲያልፍ አድርጎታል። ይህ ተስፋ በከንቱ እንዳይቀር እግዚአብሔር ወደፊት ምሥጢሩን የሚገልጥበት መንገድ ይኖራል ብለን እናምናለን።

እኚህ በቁመናቸውና በብሩህ ገጽታቸው ብቻ ሳይሆን በበጎ አድራጎታቸው በደግነታቸውና በርኅራኄያቸው በሕዝብ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆኑት ልዑል የረጅም ጊዜያት አልጋወራሽነት ዘመናቸው አገሪቱ በአጋጠሟት የፖለቲካ ማዕበል ውስጥ ሳይወዱ በግድ እንዲገቡ አድርጓቸዋል። ለምሳሌ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ወንድሟሟቾች ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይና አቶ ገርማሜ ንዋይ በአካሄዱት የክብር ዘበኛ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ እርሳቸውን ሴረኞቹ በቁጥጥራቸው ካዋሉ በኋላ የሕዝብ ድጋፍ እንዲያገኙ በማሰብ አልጋወራሹን እንግሡናል። ሲሉ አውጀዋል። እንደዚሁም በ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ግፈኛው ደርግ የመንግሥት ግልበጣ ተግባር በፈፀመበት ወቅት ለይስሙላም ቢሆን ሕዝብን ለመደለል ሲል አልጋወራሹን «ንጉሥ» ብሎ ሠይሟቸዋል። በዚያን ጊዜ አልጋወራሹ በደረሰባቸው የስትሮክ በሽታ ምክንያት ከነቤተሰባቸው ከአገር ውጭ ሄደው በሐኪምና እንግሊዝ አገር ነበሩ።

በዚህ ዓይነት ከዛሬ ፳፪ ዓመት በፊት ጀምሮ በደረሰባቸው የጤና መታወክ ምክንያት በውጭ አገር ሕክምና እንዲሹ ከመገደዳቸውም በላይ በአገሪቱ ላይ የደረሰው ከባድ የፖለቲካ ውጣ ውረድ ተጨምሮበት ብዙውን የሰቆቃ ዘመን ያሳለፉት በስደት በኃዘንና በትካዜ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። በተለይም በሕዝብ ግፊት በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በስደት እንዳሉ የንጉሠ ነገሥትነቱን ኃላፊነት ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆኑበት ጊዜ አንስቶ በየጊዜው ባሰሙት ንግግር እንደሚከተለው ብለው ነበር።

« ... የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲከበር የሕዝቡም ደህንነት እንዲጠበቅ በጠቅላላው ለአገር ዕድገትና ብልጽግና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ በመሆን ከተቀባንበት ጊዜ ጀምሮ ከገናናው አባታችን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጎን ቁመን አገራችንና ሐዝባችንን አገልግለናል። አሁንም ጥረታችንና ፍላጎታችን ሁሉ የተጀመረውን ከግቡ ለማድረስ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ሕይወታችን ደስታው ደስታችን ችግሩ ችግራችን ሞቱ ሞታችን ነው። ከሕዝባችን የተለየ የግል ኑሮ የለንም። እንዲኖረንም አንፈልግም። የምንፈልገው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላም አግኝቶ የተደላደለ ሕይወት እንዲኖረው ነው። በታወቀው ምክንያት በሕዝባችን መካከል መሆን ባንችልም በኃሳባችንና በመንፈሳችን ተለይተነው አናውቅም። በስደት ሆነን መከራውን ችግሩንም ተካፍለናል። አሁንም በሕዝባችን መካከል በመገኘት ችግሩንና ደስታውን ለመካፈል አንድም መንፈሱን ለማበረታታትና ሞራሉን ከፍ ለማድረግ ኃይሉን አሰባስቦ ታሪካዊ አንድነቱን በማደስ አገሩን በጋራ እንዲገነባ የሚገባንን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል።

ፍላጎታችን እግዚአብሔር እስከ ፈቀደልን ድረስ የተቻለንን ሠርተን ለተተኪው ትውልድ ጽኑ መሠረት በመጣል ታሪካዊ ቅርሳችንን አስረክበን የመሸጋገሪያውን ድልድይ ዘርግተን ለማለፍ ነው። ይህን የቆምንለትን ብሔራዊ ዓላማ በትክክል ግቡን እንዲመታ ለማድረግ ንጉሣውያን ቤተሰብና እንዱሁም አገር አፍቃሪ ለሕዝብ ተቆርቋሪ የሆኑ ታዋቂ ግለሰቦች አብረው እንዲሠሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። እኛም ባለንና በነበረን ታሪካችንና ባህላችን መሠረት በሕግ በተወሰነ የዘውድ መንግሥት የታሪክ ድባብ በመሆን ለማገልገል ዝግጁነታችንን እናረጋግጣለን» ሲሉ ለውድ አገራቸው ያላቸውን የዘለቄታ ዓላማና ፍቅር ደጋግመው አረጋግጠው ነበር።

በዚሁም መሠረት አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን የአባቶች ባሕልና ቅርስ እንደነበረ እንዲጠበቅና ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ በማለት ተነሣሥተው « ሞዓ አንበሳ ዘአምነገደ ይሁዳ » ...

ሆኖም «ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል» ነውና ዓፄ አምኃ ሥላሴ ምንጊዜም ቢሆን አገራቸው ተመልሰው በተወዳጁ ሕዝባቸው መካከል ለመገኘት ዝግጁ ነበሩ። በበኩላቸው ከዚህ የበለጠ የሚያስደስታቸው ነገር አልነበረም። ይህ ኃሳባቸው በሕይወት ባሉበት ጊዜ ሳይሳካ ቀርቶ አሁን በሞታቸው በመፈፀሙ ኃዘኑን የበለጠ ያከብደዋል። ይህ የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ መቀበል አለብን። ኃዘኑ መራርነቱ ለአንድ ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ፈጣሪያችን ነፍሳቸውን ከአብርሃምና ከይስሐቅ ጎን በመንግሥተ ሰማያት እንዲያኖርልን በመጸለይ እንሰናበታቸዋለን። ስለሆነም ንጉሥ ያልፋል ንጉሥ ይተካል። የኢትዮጵ ያ ዘውድ ለዘለዓለም ይኑር።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።